1437 Bannock St.
Denver, CO  80202
p: 720.865.7695
JIC_news@denvergov.org

**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**እንደደረሰ ወዲያው ይፋ የሚደረግ**

ሰኞ, አፕሪል 6, 2020

# ዴንቨር በቤት ውስጥ ቆዩ ትዕዛዝን አራዘመች፣ ከተማዋም ተደራሽነትዋን እና ሕግ ማስከበሩን ቀጥላበታለች

**ዴንቨር**–ውጤታማ በሆነ መልኩ ወዲያውኑ ከንቲባው Michael B. Hancock የዴንቨር ከተማና እና ካውንቲ በቤት ውስጥ ቆዩ የማህበረሰብ ጤና ትዕዛዝ እስከ አፕሪል 30/2020 ድረስ ተግባራዊ እንዲሆን አራዝመዋል፡፡ በተጨማሪም ከተማዋ በርካታ ሰዎች የሚሳተፉባቸው ስብሰባዎች ላይ የተጣለው እገዳ እስከ አፕሪል 30 ድረስ እንዲራዘም እንዲሁም የየእለቱን የአደጋ ክስተት የተመለከተ ሪፖርት በ denvergov.org ላይ ይፋ ማድረግ የሚጀምሩ ይሆናል፡፡

“የዴንቨር ነዋሪዎች በቤት ውስጥ በመቆየት እንዲሁም አካላዊ ርቀታችሁን በመጠበቃችሁ ኮርቼባችኋለሁ፣ ላመሰግናችሁም እወዳለሁ” ብለዋል ከንቲባው ሀንኮክ በተራዘመው ትዕዛዝ ዙሪያ ንግግር ሲያደርጉ፡፡ “ለአብዛኞቻችሁ ቀላል እንደማይሆን አውቃለሁ፤ ነገር ግን በማህበረሰባችን እንዲሁም በሀገራችን የኮቪድ-19 ስርጭትን አስመልክቶ አሁን ላይ በባለሙያዎች የሚሰጡ ቁጥሮች እና ምክሮችን መተግበር በበሽታው የሚያዙ ሰዎች ቁጥር እንዲቀንስ እና በተቻለን ሁሉ ጤናችንን እንድንጠብቅ የሚያደርገን ነው፡፡”

ዋናው ትዕዛዝ በአፕሪል 11 ተፈፃሚነቱ እንዲያበቃ ነበር የተወሰነው፡፡ ትዕዛዙን ማስቀጠልን በተመለከተ ተጨማሪ መልዕክቶችን እና አስገዳጅ ሁኔታዎችን ከንቲባው ለሁሉም ነዋሪዎች አስፈላጊ ለሆኑ ግብይቶች አሊያም ወሳኝ ለሚባሉ እንቅስቃሴዎች ካልሆነ በስተቀር በቤታቸው እንዲቆዩ አሳስበዋል፤ በዚህም እየከፋ የመጣውን የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ተከትሎ የማህበረሰብ ጤና ትዕዛዝ መመሪያን በማገበብ ራሳቸውን እንዲጠብቁ መክረዋል፡፡

ዛሬ ይፋ በሆነ መረጃ በዴንቨር፡-

- 6,090 በቤት ውስጥ ቆዩ የሚለውን ትዕዛዝ ማክበርን በተመለከተ ከነጋዴዎች እና ከነዋሪዎች ጋር ግንኙነት ተፈጥሯል
- 1,796 ማስጠንቀቂያዎች
- 14 መጥሪያዎች ነበሩ

ለተጨማሪ መረጃ አባሪ የተደረገውን ክልከላ የተደረገባቸውን ነገሮች ዝርዝር ያካተተውን የማሕበረሰብ ጤና ትዕዛዝ ይመልከቱ፡፡

የየዕለቱ አሁናዊ ሪፖርት በየቀኑ የሚዘጋጀው በከተማው የኤመርጀንሲ ኦፕሬሽን ሴንተር (EOC) ሲሆን የፌዴራሉን የአደጋ ጊዜ አስተዳደር መመሪያን መሰረት አድርጎ ያዘጋጃል፡፡ ዛሬ ሪፖርቱን ማየት ከፈለጉ denvergov.org ላይ Local Preparation and Coordination በሚለው ገፅ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡

እለታዊ ሪፖርቱን በኢሜላቸው መቀበል የሚፈልጉ የሚዲያ አካላት አድራሻቸውን በ JIC_News@denvergov.org መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ በዴንቨር በኮቪድ-19 ዙሪያ በየጊዜው የሚወጡ ምላሾችን ለማግኘት denvergov.org ን ይጎብኙ፡፡

###